የአንድነት ሥራ አስፈፃሚ ኮሚቴ በ_6/09/01ዓ.ም በአንድነት ጽ/ቤት ከቀኑ 7 ሰዓት አስከ 8 ሰዓት ባደረገው አስቸኳይ ስብሰባ 13 አባላቱ ተገኝተው ወ/ት ብርቱኳን ሚደቅሳ ከእስር እንዲፈቱ ለማጠየቅ ሰላማዊ ሰልፍ እንወጣ ወይስ አንወጣ በሚል ጉዳይ ላይ ተወያይተው አለመግባባት በመፈጠሩ ጉዳዩን እንደሚከተለው ወስነዋል፡፡

| ተ.ቁ | ሰላማዊ ሰልፍ እንወጣ | መውጣቱ የለብንም | ድምፀ ተዓቅቦ ያደረጉ |
|---|---|---|---|
| 1 | ዶ/ር ሃይሉ አርአያ | 1.ኢ/ር ግዛቸው ሽፈራው | 1. ወ/ሮ ላቀች ደገፋ |
| 2 | አስራት ጣሴ | 2.ዶ/ር ያዕቆብ ሃ/ማርያም | 2. አሰፋ ዳኜ |
| 3 | አክሉ ግርግሬ | 3. ብሩ ብርመጂ | |
| 4 | መስፍን ሽፈራው | 4.እንዳልካቸው መኮንን | |
| 5 | ንጉሴ ነወጤ | 5.አስቻለው ከተማ | |
| 6 | ታምራት ታረቀኝ | | |

ሰላማዊ ሰልፍ እንወጣ ያሉት እነ ዶ/ር ሃይሉ አርአያ ዝም ካልን እንደሸንፈት ይቆጠርብናል፣ በወጪ ያሉት ተቃዋሚዎች የኛን ችግር አይረዳም፣ ሩቅ ሆነው የሚጠዬቃቸው የለም፣ ተኛችሁ እንደ አደኢፓ ልትሆኑ ነው ወይ እያሉ አስቸገሩን፣ ብርቱኳንም በእናትየዋ በኩል ረሳችሁኝ ግድ የለም ብላ እንዳዘነች መልዕክት ልካብናለች፣ ስለዚህ አንዴ ወጣ ብለን ብነ ስርዓት ጠዬቀን ብንገላገል ይሻለናል በማለት ሃሳባቸውን ያቀረቡ ሲሆን፣

ሰላማዊ ሰልፍ መውጣት የለብንም ያሉት እነ ኢ/ር ግዛቸው የማግስት አካሄድ አደገኛ ነው፣ በዚህ ሰበብ በህግ ሊጠዬቀን ይችላል፣ ፓርቲውንም ለዘጋው ይችላል፣ ስለዚህ ባሉን ሌሎች አማራጮች ተጠቅመን ብንታገል ይሻላል በማለት የተቃወም ሃሳባቸውን ገልፀዋል፡፡ ድምፀ ተዓቅቦ ያደረጉት ደግሞ በጉዳዩ ላይ በዙም አስተያየት ያልሰጡና በወይይቱ ደስተኛ ያልነበሩ ናቸው፡፡

በመጨረሻም በነገው ዕለት በ8/09/01 ዓ.ም በሚደረገው ሰላማዊሰልፍ የሚበብ የተዘጋጀ ጽሁፍ ቀርቧል፡